# እንደ ጨጓራ የፖለቲካ ሽንፍላም ቢያጥቡት አይጠራም

ማርቆስ ደጀን

ለወያኔ በስልጣን መክረም በጣም ከጠቀሙት ክስተቶች አንዱ የፖለቲካውን መድረክ በሽንፍላ ቅጥረኛችና ከፋፋዮች ሊያጨናንቅ መቻሉ መሆኑ ያድባባይ ምሥጢር ነው። እኛም "ብልጥን እባብ አንድ ጊዜ ይነክሰው ይሆናል፤ ሞኝን ግን ሁለት ጊዜ - አንድም ሳያየው፣ ሁለተኛም ከዚህ ጋር የነደፈኝ ብሎ ሲያሳይ እሚለውን ይትብሃል" ልብ ማለት ተስኖን እየተጃጃልን ተመችተንለታል። ድንግርግርና ውዥንብር በሰፈነ መጠን የተቃዋሚዎቹ ጎራ ይፈረካከሳል፤ ከስህተታችን በመማር ፈንታ በስህተታችን ተስፋ ቆርጠንም፣ ወደ ተስፋ አስቆራጮቹ አምባ የእርድ በሬ ሆነን የምንሄድ አለን።

ወደ ዝርዝሩ ገብቼ አካፋን አካፋ ከማለቴ በፊት ግን በቅድሚያ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ይህን የወያኔን ተንኮል እያገዙ ያሉትን ክፍሎች መጠቆሙና መውቀሱ ተገቢ ይመስለኛል። የሹም ዶሮ ነን ለምንስ ተነክተን እሽ ተብለን አይሉም ብዬ በመገመት፤ መደማመጡን፣ ስህተትን መመለካከቱ ለጋራ ጥቅም ነውና።

ቅንጅት ለልደቱና ኢዴፓ መሸጋገሪያ እንደሆነው ዓይነት፤ አብዛኞቹን የወያኔ ሽንፍላዎች መድረክና ድምጽ በመስጠት ጎጂ ሚና የተጫወተው ኢሳት የሚባለው ድርጅትና ባለቤቱ ግንቦት 7 ቡድን ነው። ተስፋዬ ገብረአብ የተባለው የወያኔና ኋላም የሻዕቢያ ተቀጣሪ የሆነውን አወናባጅ ታጋይ ብሎ ያናፈሰለት ግንቦት 7ና መገናኛ ብዙሃኑ ሲሆኑ ለግለሰቡ መጽሐፍም መግቢያ የፃፈለት የግንቦት 7 ዋና ሊቀመንበር ነበር። ይህን ተከትለውም ሌሎችም "ታጋዩ ተስፋዬ!" ብለው ሲያውድሱት እንድነበር የሚረሳ አይደለም። ሀገር ወዳዶች ግን የዚህን ከሃዲ ሚና በሚገባ አጋልጠው፣ ይኸው ጥጉን ይዟል። ኋላ የወያኔ ሰላይ ተብሎ ሊብጠለጠል የበቃውንም የአውራምባ ታይምስ አዘጋጅ--ዳዊት ከበደ-- በኢሳትና ግንቦት 7 ትልቅ ድጋፍንና መድረክ አግኝቶ ሲጨበጨብለት እንደነበር ይታወሳል። ለጽንፈኞችም መድረክ ሰጪም ኢሳት ነው። የቅርብ ጊዜ ምሳሌ መስጠት ይቻላል፤ እብዱን ጃዋር መሃመድን። ይባስ ብሎ ደግሞ ይኸው ኢሳት፣ መሰሎቹን አስከትሎ፣ ለወንጀለኞች ፤ ለነ ኮለኔል መንግስቱና የደም አባሪዎቹ መድረክ ሰጥተው ሕዝብን አበሳጭተዋል። ለነፍሰ ገዳዮች መጽሃፍ ኣታሚዎቹም የሚጠቀሱ ናቸው። ይህ ሁሉ ለወያኔ በጣም ረድቶታል። መጋለጥ፤ መወገዝና መቆም ያለበትም ነው፣ የኢትዮጵያንና የጉስቁል ሕዝቧን የመከራ ቀን እናሳጥር የምንል ከሆነ። ስለዚህም አካፋን አካፋ ለማለት ነውና ዛሬ ብዕሬን ያነሳሁት፣ ልብ ያለው ልብ ይበል፡

## 1/ ተመስገን ደሳለኝ ወይስ ዳግማዊ ልደቱ?

የሕዝብ ጎራ አባል አስመስለው ወያኔም ኢሳትም፤ ኢትዮሚዲያና ሌሎች ድረ ገጾች ሲያቀርቡት የቆዩት የመንግስት ሰራተኛና የድንገት "ጋዜጠኛ" ተመስገን ደሳለኝ የሚባለው ነው ። ይህ ግለሰብ ሲሰራ የቆየውና አሁንም እየሰራ ያለው በጥቅሉ ለወያኔ፣ በተናጠልም ለስብሓት ነጋ ጥቅም ነው። በመግቢያዬ እንደጠቀስኩት፣ ብዙ ሰው ለወያኔ የተንኮል ስራ እንግዳ ነው እስካሁን። ሰው ታስሮ ከተፈታ ጸረ ወያኔ ይመስላቸዋል፤ ወያኔ አጠቃሁት ሲልም ግለሰቡ የምር ለወያኔ የመቀመጫ እሾክ የሆነበት ይመስላቸዋል። ይህ ግን አንዳንድ ጊዜ ስህተት ነው፣ ሰርጎ ገቦችን ማዘጋጀትና ሽፋን መስጫ ስልት መስጠት የጠላት ወገን የሚጠቀምበት አንዱ ከውስጥ ሆኖ ማጥቂያ መንገድ ዘዴ ነውና። ከቅርብ ጊዜ ክስተታችን ምሳሌ ልስጥ። ልደቱ ለይስሙላ ለወር ታስሮ በቀባጣሪዎችና ጅሎች ማንዴላም ተብሎ ነበር። ተለሳልሶና አስመስሎ ግን ያው የሕዝብን ትግል ማጅራት መቶ ለወያኔ ጠቀመ። ተመስገን ደሳለኝ ደፋሩ አቦይ ለሚለው ለስብሐት ነጋ ያደረ መሆኑ በመረጃ ሊረጋገጥ የሚችል ነው። በጭፍኑ ባደባባይ ሊወይን ቢነሳ፣ ለተሰጠው ስራ ጠቃሚ አይሆንምና አልፎ አልፎ ወያኔን ማውገዙ የሚጠበቅና እያደረገውም ያለ ነው። ዋናው ትኩረቱ ግን ታጋዩን ጎራ መውረፍና ማጥቃት ነው። በዚህም መሰረት ተመስገን ደሳለኝ በተደጋጋሚና በተለይ ለምሳሌ ኢሕአፓን፣ ያን የታገለ ትውልድና አሁንም ወያኔን አምርረው የሚታገሉትን ሲያጠቃ ቆይቷል። አሁንም ቀጥሎበታል፣ የተሰጠው የቤት ሥራ ነውና።

ተመስገን ለይስሙላ ክስ ይመሰረትበታል፣ ግን መቼም ሲፈረድበት ወይም ሲታሰር ሰምተንም አናውቅም፣ ሌላው ቀርቶ ለሽፋን እንኳን ቢሆን። የተመስገንን ሚና በሀገር ውስጥ የሚታተመው ሎሚ መጽሄት ቁጥር 46 ለኢሕአዴግ "'ማስተንፈሻ' ማነው?" ብሎ በሚገባ ተችቶታል። የተመስገን ጋዜጦች ሲዘጉ ወዲያው በሌላ የተመስገን ጋዜጦች ይተካሉ። ገንዘቡ ከዬት እንደሚመጣ ምስጢር መሆኑ ነው። ፍትህ፤ ልዕልና፤ አዲስ ታይምስ፤ ወዘተ በማለት ተመስገን አንዱን በሌላው እየተካ ሲቀጥል--እንዲቀጥል ሲፈቀድለት-- ሌሎች ግን በታገዱበት ተዘግተው ቀርተዋል። የተመስገን ልደቷዊ ሚና ምንም ጥርጥር ውስጥ የማይከት መሆኑን መረዳት የሚቻል ነው። የሎሚው ጽሁፍ አቅራቢ ሱራፌል ወ/ገብርኤል ካቀረበው ጽሁፍ በሰፊው እስቲ ልጥቀስ፡

*"የመታበይ (የተመስገን) ፤ የእብሪትና ከእኔ በላይ ለአሳር" መልዕክት ጠቅሼ ወደ ነገረ ጉዳዩ ልንደርደር።*

*"በወቅታቸው የሀገሪቱ የሕትመት ስርጭትን በቀዳሚነት ይመሩ የነበሩት ፍትሕ ጋዜጣና አዲስ ታይምስ መጽሄት ያለአግባብ እንዲዘጉ የተደረጉት አምባገነኑ ኢህአዴግ ከራሱ ድምጽ በቀር ምንም አይነት ይዘት ይኑረው፤ በየትኛውም ደረጃ ያለ ይሁን የተለየ ድምጽ መሰማቱን ያለመፈለጉን የሚያሳይ ነው። ይህ ባህሪው ከምላ ጎደል የተሻለ የሚባል ጥንካሬ የነበራቸውን የህትመት ውጤቶች በመዝጋት ------- ጥቂት*

*ደካማ ሚዲያዎችና በርካታ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የሚቆጣጠራቸው የራሱ ሚዲያዎች ብቻ እንዲኖሩ በማድረግ ቀን ከሌሊት በፕሮፓጋንዳ ስራ ተወጥሯል”*

*“ ከላይ በትምህርተ ጥቅስ የሰፈረው ማብራሪያ የተወሰደው በተመስገን ደሳለኝ ማኔጂንግ ዳይሬክተርነት ከሰሞኑ ለህትመት ከበቃው አዲሱ “ ልዕልና” ቁጥር 2 ጋዜጣ ነው። እሱ ከሚያዘጋቸው ጋዜጦች በስተቀር ሌሎች የህትመት ውጤቶች “ደካማና የኢሕአዴግ ተጧሪ” መሆናቸውን አዲስ ታይምስ ከሕትመት በተቋረጠችበት ሰሞን ተመስገን ደሳለኝ በኢትዮ ማህደር ጋዜጣና በሌሎች ሚዲያዎች ያለመታከት የደጋገመው በመሆኑ የግለሰቡ አቅዋም መሆኑን አምኜ ለመቀበል ተገድጃለሁ። የኢትዮጵያ ነጻ ፕሬስ ታላቅ ተጋድሎ እስከከፈለበት ምርጫ 97 ድረስ በአንድ ጋዜጣ እንኳ መጣጥፍ ሲያቀርብ ያልተስተዋለውና ብዙዎቹ ሚዲያዎች የኢሕአዴግ አፈና ሰለባ ሆነው ከጨዋታ ውጪ ከተደረጉ በኋላ በድንገት ከሰማይ የወረደ አርበናኛ ለመሆን የታደለው ተመስገን ደሳለኝ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ነበር። (ስርዝ የታከለ) … በፍትህ ጋዜጣና በአዘጋጁ ላይ ከ 34 ክሶች በላይ እንደተመሰረተባቸው በፕሮፓጋንዳ መልክ ይገለጽ እንጂ በግለሰቡም ሆነ በጋዜጣዋ ላይ የደረሰ የእጉዳ እርምጃ ግን አልነበረም።”*

እስከ ዛሬም የለም። በወያኔ ውስጣዊ ንትርክ ሂደት ውስጥ ተመስገን ከስብሓት ጋር በመሆኑ በበረከት ስምኦን ታግዶ ነበር። ወያኔ ማለዳን፣ እፎይታን (የተስፋዬ ገብረአብ እጅ እጅ ያለ መፈንጫ)፤ኢፍቲን ወዘተ ጋዜጣ ብሎ ያትም ነበር። አይጋ ፎረም፤ ትግራይ ኦን ላይን ወዘተ የሚሉም ማፈሪያ ድረ ገጾች አሉት። ጭሌው የወያኔ አሽከር ተመስገን ቢሮዬ በወያኔ ስለምትከበብ አሲምባ ብዬ ጠራኋት ብሎ ያሾፋል ። በሰማዕትና በደማቸው መቀለድ ነውና ተልዕኮው ። ሐበሻ ረቪው የተባለውን መጽሔት ወያኔ ሲያግድ እነ ተመስገን ስም እየቀያየሩ ሲመጡ አላገዳቸውም። ለሲሳይና እስክንድር ፈቃድ ያገደው ወያኔ ለተመስገን ግን ፍቃድ ሰጥቶ አሁንም እያሰራው አለ። የሎሚ መጽሔት ጽሁፍ እንዳቀረበው ደግሞ ጋዜጠኛ አለማየሁ ባዘዘው ሁሉን መስፍርት አሟልቶ “ጊዜያችን” የሚል መጽሄት ሊያወጣ ሞክሮ አልተሳካለትም። ከላይ መጥቀስ ጀምሬው የነበረው ጽሁፉ ከዚህ ጋር በተያያዘ ትዝብቱን በመቀጠል ያሰፈረው እንዲህ በማለት ነው፡ *“እሱ [ጋዜጠኛ አለማየሁ] ይከልከል እንጂ፣ የገዢው ፓርቲ የአንቀልባ ልጆች ግን ሚሊያ ሲቀያይሩ ቢከርሙ ፈቃድ እንከለከላለን የሚል ቅንጣትም ስጋት የላቸውም ።”*

ታሪክንና የወያኔን ተንኮል ለዘነጉ ደግሞ የሎሚው ጽሁፍ የሚከተለውን ብሏል፡

*“ በኢትዮጵያ ታሪክ ሊሆኑ አይችሉም የሚባሉ ሁኔታውች ካለፉ በኋላ ሲገለጡ ጉድ ያሰኛሉ፤ አሰኝተዋልም። አንድ ምሳሌ ብቻ እንጥቀስ………*

*ጊዜው 1984፤ ኢሕአዴግ ስልጣን ቢጨብጥም እርካቡን አላደላደለም ነበር። በዚህ ወቅት ነበር ብሄራዊ ደሞክራሲያዊ ህብረት የተሰኘ ተቃዋሚ ፓርቲ ህዝቡን ማስተባበርና ከፍተኛ ለውጥ ማሳየት የጀመረው። የፓርቲው ዋና ጸሓፊ ኤርትራዊ ሆኖ ሳለ "እኛ ኢትዮጵያውያን እንጂ ኤርትራውያን አይደለንም" የሚል መፈክራቸው በርካታ ደጋፊዎችን አስገኘላቸው። ድርጅቱ የሚጠራቸው ስብሰባዎችም በህዝብ ጎርፍ ይጥለቀለቁ ጀመር። በመጨረሻስ? የፓርቲው ዋን ዋና ጸሐፊ የሻዕቢያ ሰው! ፕሬዚዳንቱም የሕወሓት ካድሬ ሆነው ተገኙ። በዚህ ፓርቲ አማካኝነት ኢሕአዴግ የሕዝቡን ውጥረት ካስተነፈሰ በኋላ ቀንደኛ አፍቃሪ ኢትዮጵያ የተባሉ ኤርትራውያንና ኢትዮጵያውያን ታድነው ተመነጠሩ። እየተያዙም ታሰሩ፣ የታሰሩት ኤርትራውያንም ለሻዕቢያ ተሰልፈው ተሰጡ። ከዚያ በኋላ ማስተንፈሺያው ፓርቲም ከሰመ። ታዲያ ኢሕአዴግ ዛሬስ ማስተንፈሻ ጋዜጣ አያስፈልገውም እንዴ? "*

ቀደም ሲል በተነሳውና ወያኔ ለማስተንፈሻነት በቀየሰው ፓርቲ ስብሰባ ላይ በመንገድ ትራንስፖርት እና በሙብራት ሃይል የመሰብሰቢያ አዳራሾች ለሚገኘው ህዝብ "ሲሞቅ በማንኪያ፣ ሲቀዘቅዝ በእጅ እንዲሉ፣ ሻዕቢያ ኤርትራ የግላችን፣ ኢትዮጵያ የጋራችን ብሎ የሀገራችንን ሀብት እየዘረፈ ነው …" እያለ በመቀስቀስ ቀን ቀን ያስጨበጨበባቸውን እጆች ማታ ማታ ያሳስር የነበረው ግለሰብ ሁዋላ ላይ ስንት ሰው አስለቅሞ፣ ስንትና ስንት ብር ሰብስቦ ተሰወረ። በንግድ ዓለም ተሰማራ።

ተመስገን ደሳለኝና የእሱ አዳናቂዎች ሚናም ማስተንፈስ ነው ። ተመስገን ነጻ ጋዜጠኛ ሳይሆን የወያኔ ቅጥረኛ ማስተንፈሻ አስመሳይ ጋዜጠኛ ነው። ዳግማዊ ልደቱ ነውና መጋለጥ ያለበት ከህዷ!

**2/ <u>ኢያው ሌንጮና የጃራው ጭራቅ ጃዋር</u>**

የዝቅጠትና ውርደት -- ቅሌት - ልክን ክብረ ወሰን በየጊዜው ከፍ (ዝቅ?) የሚያደርገው ሰው ማነው? ቢባል እና ሌንጮ ለታ ቢባል ተገቢ ነው። ሌንጮ የኦነግ ዋና መሪ ሆኖ የዚህን ድርጅት ጽንፈኛና የግንጠላ አቋም ያስረገጠ ግለሰብ ነው። በደርግ ጊዜ ከዚያ አረመኔ መግንስት ጋር ሰርቷል። ደርግ ተለጣፊዎቹን ሊመታ ሲነሳ ደግሞ ፈርጥጦ ከባሮ ቱምሳ ጋር ራሱን ሼክ ጃራ ብሎ ከሚጠራ ጽንፈኛ ጎራ ተደባልቆ ነበር። ሼክ ጃራ ጠላቶቼ ክርስቲያኖች፤ አማራዎች፣ ክርስቲያን ኦሮሞዎች ወዘተ ብሎ የሚፈርጅ፤ በሳውዲና በሱዳን የሚደገፍ ጸረ ኢትዮጵያ ነፍሰ ገዳይ (ባሮ ቱምሳንም ገድሎታል) ግለሰብ ነበር። ሌንጮ ከእሱ ጋር ሰምሮ ከርሞ፣ ባሮ ከተገደለ በኋላ ወደ ሶማሊያ ሄዷል። ከዚያም በሻዕቢያ ስብሳቢነት ካርቱም መጥቶ ለሻዕቢያ ያደረውን ኦነግ ሲመራ ይቆይና ለዚያን ወቅት የኦነግና የሻዕቢያ ወንጀል (በአሶሳ የአማራዎች ጭፍጨፋ) ተጠያቂ የሆነ ግለሰብ ነው። ሌንጮ ለደርግ እንዳደረው ሁሉ ለወያኔም አድሮ መከረሙ ሀቅ ነው። የወያኔ ጦር የሽግግር መንግስት ተብዬው ጦር እንዲሆን እጁን ሰቅሎ በራሱ ላይ የስቅላቱን ገመድ ያሰረ ጸራ አማራነቱ ያወረው ሰው ነው። ሻዕቢያንም ደግፎ አስመራ ድረስ ዘልቆ፣

የለፈፈውን ጸያፍ ነገር ሁሉ ሕዝብ የሚረሳው አይደለም።  ለአርባ ጉጉ ፍጅት ባይሆን እንኳን፣ ለአሶሳና በደኖ ፍጅት ቀጥተኛ ተጠያቂነትም አለው፡፡  ብዙ ሺ የኦነግ ኣባላትና ደጋፊዎችን አሳስሮ፣ መለስ በሰጠው የመውጫና የማዋረጃ ቪዛ ተጠቅሞ፣ በሻዕቢያው አምባሳደር አቅራቢነት ዲማ ነጎን ይዞ፣ መለስን ተሰናብቶ እና አብሮም ተለቃቅሶ፣ ስደት የወጣ ክብር አልባ ፍጡር ነው።  ብዙ መጨመርም ይቻላል።  አቋም የቀየረ ቢያስመስልም ያው ጠባብና ልገንጠል ባዩን የኦነግን አቋም በሪፈሬንደም ጠቅልሎ የዋጠና ሊያስውጥ የሚጥር ነው። ሌንጮ ዛሬ በ እስራኤልና አሜሪካ ቅጥረኛው ኤፍሬም ይስሓቅ አስታራቂነት ወደ ወያኔ ሊገባና ሊያድር (ሊነጠፍ) የወሰነው ወያኔ ውጥረት ውስጥ ስለገባ፣ የወያኔን ጸረ አማራ ዘመቻ ለመደገፍና ለማጠናከር ብቻ ነው። ለሌንጮ የፖለቲካው አልፋ ኦሜጋ ጸረ ኣማራነትና ስልጣን ሹመት ፍለጋ ብቻ ነው።

በዚሁ ርኩስ ዓላማ የሚያጅበው በጫት ይሁን በሌላ ያበደው፣ የአሜሪካንና የወያኔም ቅጥረኛ የሆነው ጃዋር መሃመድ የሚባለው የበሽተኛው ሼክ ጃራ ተከታይ ነው። ጃዋር በስታንፍሮድ ዩኒቨርስቲ (አሜሪካ) ያለፈ ነውና ለአሜሪካ የስለላ ተቋም (ከዚህ ተቋም ብዙዎች ይመለመላሉና) ተገዢ ቢሆን አያስገርምም። ስራው ግን ባመዛኙ ያግልጋያቸው የወያኔ ተልዕኮ ያለው ያስመስለዋል። በሕዝብ መሀል--ቢያንስ በውጭ ሀገር ባለው ኢትዮጵያዊ ዘንድ-- ሰፊ ክፍፍልን በብሄረሰብና በሃይማኖት ደረጃ ማስፈን ነው። ይህ ደጎም ወያኔ የሚፈልገው ነው። ጃዋር በአማራውና በክርስቲያኑ ላይ የሚያቀረሸው ማንነቱን ሲገልጸው ጸረ ወያኔነቱ ግን የይስሙላ መሆኑን ማንም የሚስተው አይደለም። ይህን ባለጌና ደም የጠማው ግለሰብ ኢምንት ማድረግ ወይም ቀጣሪው ወያኔ እንደሚለው ማምከን ያስፈልጋል። ከእንግዲህ ለዚህ ልፍስፍስ ጸረ ህዝብ መድረክ የሚሰጡ ሁሉ ጸረ ኢትዮጵያ ናቸው ቢባል ማጋነን ወይም ማከረር አይሆንም። ፍጅት ጠሪ በመሆኑም መከሰስ አለበት። የእሱ አርአያ--ራሱን ሼክ ጃራ የሚለውና ቀደም የዚያድ ባሬ ሎሌ ሆኖ እነ ባሮ ቱምሳን ሁሉ የገደለው ጠላቶቹን ሲዘረዝር አንደኛ አማራ፤ ሁለተኛ ክርስቲያን ኦሮሞ፤ ሶስተኛ ደርግ ወዘተ ይል እንደነበር መታውስ ያለበት ነው። ጃራ እንኳን ጠመንጃ ይዞ ጫካ ገባሁ ያለና  የ አሰቦት መነኮሳትን ጨፍጫፊ  የነበር ሲሆን ይችም ሰይጣናዊ "ድፍረት" ከጃዋር ዓይነቶቹ የምትጠበቅ አይደለችም።  ጎራዴ ይዞ ፎቶ መነሳት ሌላ! ባሩድ በሚጤስበት ዘው ማለቱ ሌላ! ለመሆኑ ለነጃዋር ዓይነቶቹ ቡከኖች አማራው እንደ ሕዝብ ሊታረድ አንገቱን ይሰጣል ያላቸው ማነው?

**<u>3/ ኤፍሬም ይስሓቅ</u>** <u>---</u> ይህን ግለሰብ በተመለከተ አንድ ዜጋ ቀደም ሲል በዝርዝር ጽፎታልና የምመለስበት አይሆንም። ግለሰቡ ግን ለአሜሪካና እስራኤል ያደረና ለወያኔም ሙሉ አገልጋይ የሆነ፤ የወያኔንም ዘረኝነት የሚጋራ ጸረ ኢትዮጵያዊ ነው።  ይህ ሀቅ ሳይሸፋፈን መነገር ያለበት ነው። አስታራቂ ሽማግሌ በሚል ሽፋን ይጠቀማልና "ወግድ አንተ ወያኔ!" መባል አለበት።

**4/ ፕሮፌሰር መሳይ--** ይህ የደርግ ኢሰፓ ሰማያዊ ለባሽና ማካሮቭ ታጣቂ ግለሰብ ድርጅቱንም ሀገርንም ጥሎ ወደ አሜሪካ ከሸሸ ጀምሮ ታሪኩን ለመፋቅ ሲፍጨረጨር መታዘባችን አልቀረም። ያን የታገለ ትውልድ በማውገዝ (ከእኔ በላይ ማርክሲስት ለአፈር ይል የነበረውን ክዶ) ራሱን ም ታሪኩንም የሚክደው አልበቃ ብሎ አሁንም የወያኔን ማደናገሪያ መርህ በመቀበል፣ የዕርቅና ሰላም አማራጭ መንግስት ምስረታን ይሰብካል። ዳግም ተሞኙ፣ ዓይናችሁን ሳትጨፍኑ በመቃዣት ተቆጠቡና ተጃጅላችሁ መጭ እድላችሁን ለሌላ ጥፋት ስጡ ነው እያለን ያለው። ይህ የዚያ አረመኔ አገዛዝ ዋና ካድሬ የነበረ እንደ ንጹህ ዜጋ ሊመጻደቅብን መፍቀድ የለብንም። ከመሰሎቹ ጋር ሆኖም በአሜሪካ ምድር መንግስትም ህገ-መንግስትም ላፅድቅላችሁ እያለ በማሾፍ በትግላችን ላይ ለመሳለቅ የሚያደርገውንም ጥረት ከትቢያ መደባለቅ ይጠበቅብናል።

**5/ ብርሃኑ ደቡር** የዚህን ርካሽ ግለሰብ ስም መጥራት ራሱን እንደ ክብር ሊቆጠር ይገባዋልና ሳነሳው እየቀፈፈኝ ነው። ይህ በመርካቶ በቀይ ሽብር ቀጥተኛ ተሳትፎ ያደረገ ወንጀለኛ ላለፉት 22 ዓመታት በወያኔነት (አባ መላ) ተደብቆ፤ በ97 በወያኔ የተገደሉትን ሳይቀር በጥፋት እየወነጀለ ለ ዘረኛው ወያኔ መሳሪያ ሆኖ የቆየ ግለሰብ በወያኔ ረቂቅ የማወናበጃ ተልዕኮ አቅዋም ቀየርኩ ብሎ እንደገና ብዙ ሰው በማወናበድ ላይ ነው። በውጭ ሀገር ነዋሪ ዜጎች ምንኛ ተላላ እንደሆኑና አዙሮ ትላንትን ማየት እንዳቃታቸው ዋናው ገላጭ ይህ ነፍሰ ገዳይና ወያኔ አሁንም ያገኘው አድማጭ መኖሩ ነው።

እስከመቼ መደናገርና ራሳችንን መጉዳት እንፈቅዳለን? ጃዋር ጀኖሳይድ ብሎ በአጼ ምኒሊክና በአማራው ላይ አረፋ ሲደፍቅና በወያኔዎች ታጅቦ ሲሳደብ፤ ብርሃኑ የተባለው የወያኔ ጨለማ ደግሞ ጸረ ወያኔ ነኝ ብሎ ይቧርቃል። ይህንንም ግለሰብ መድረክ የሰጠውና ለሴራው የተባበረው (አውቀው ይሆን ሳያውቁ) ኢሳት ነው። ኤልያስ ወንድሙ የተባለ የደርግ ሎሌም ለነፍሰገዳዮቹ የብዕር ኩሊ አታሚ ሆኖ ብቅ ሲልም መድረክ ሰጪው ይሀው ኢሳት ነው። ይህ ሁሉ በሀሳብ ነጻነት ወይም በፕሬስ ነጻነት ሊፈረጅ የሚችል አይደለም። ትግልን እየጎዱና ሕዝብን ዳግም እያቆሰሉ ያሉትን ማገዝ፣ ሕዝብንና ትግልን በተጨባጭ መጉዳት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። መድረክ መከልከል ብቻ ሳይሆን ጸረ ህዝቦች እስትንፋስ ሊነፈጉም ይገባል። የሽብርተኛ ክስ ተመስርቶባቸው ዘብጥያ የወረዱትን እነ እስክንድር፤ ርዕዮትና ውብሸትን እያደነቁ በዚያው ደግሞ እነ ተመስገን ደሳለኝ ዓይነቶቹን ለማዳነቅ መነሳት እንደ ወያኔ መቀለድ ነው። ማን ከሕዝብ ጎራ አለ? ማን ደግሞ በማጭበርበርና በማስመሰል ተጠግቶ ጉዳት እያደረሰና ሊያደርስ እያሰላ ነው የሚለውን ማውቅ ያስፈልጋል። አለበለዚያ ወያኔ በስልት እየቀለደብንና እያተራመሰን በጫንቃችን ላይ ከበሮ እየመታ ይደንስብናል። ከዚህም ተያይዞ መታውቅና መታመን ያለበት ለሕዝብ ጠላቶችና ለወያኔ ቅጥረኞች አክብሮትም ለቀቅተኝነትም ሊኖረን፣ ልናሳይ እንደማይገባ ነው። ትግሉን እየጎዱ ያሉትን ሁሉ ማጋለጥና ከጎራችን ማራቅ፣ ማስወገድ የግድ ይሆንብናል፤ ሊሆንም ይገባል።

የሎሚው ጽሁፍ ስለ ተመስገን ደሳለኝ በጻፈው ላሳርግ፡ እንዲህ በማለት፡-

*" ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በተደጋጋሚ ለወራት በጨለማ ቤት እስር እንዲቆይ ተፈርዶብታል። እየወለቀ የሚያስቸግረው እጁ የተሰበረውም በድህንነት ሃይሎች ድብደባ ከተፈጸመበት በኋላ ባዶ የስሚንቶ ወለል ላይ ለቀናት እንዲተኛ በመደረጉ ነው። ሌሎችን በወያኔ ደጋፊነት የሚከሰው ተመስገን ደሳለኝ አቶ መለስ ዜናዊ እስኪሞት ድረስ እንዲህ እየፈነጨ እንኳንስ አንድ ቀን ሊታሰር ዝንቡን እሽ የሚለው አልነበረም። አቶ መለስ የሞተ ሰሞን ግን የሰውዬውን የሞት ዜና የያያዘው ጋዜጣ እንዳይታተም የከለከለው የገዢው ፓርቲ ወገን* (ከደሳለኝ አለቃ ከስብሓት ተጻሮ የነበረው በረከት) *ለአምስት ይሁን ስድስት ቀን ቃሊቲን ጎብኝቶ እንዲወጣ አድርጎታል። ስድስት ቀናት የቆየበትን የወህኒ "ጀብዱ" ድርሳን ሲተርክልን ግን ይኸው ስድስት ወር አለፈ። ካደረሰን ስድስተኛው ዓመት ድረስ ይቀጥልም ይሆናል"።*

ቀጥሏልም። አዳማጭም አላጣም። ሲያወናብድ በርታ የሚሉትም አልጠፉም። እስከመቼ ወያኔና ቅጥረኞቹ አሊያም የባዕድ ቅጥረኞችና ጸረ ሕዝብ ወንጀለኞች ያደናግሩናል? ይጎዱናል? ነጋ ጠባ ለአወናቦጆችና ዘረኞች ሰለባ መሆን ሀገርን ያሳጣልና ይታሰብበት።

ለወያኔ ጸረ ኢትዮጵያ ዕቅድ ሰለባ አንሁን!!!

ልብ ያለው ልብ ይብል።